# ኢትዮጵያችን

*አንድ ሀገር! አንድ ሕዝብ! ኢትዮጵያችን ሕዝባዊ ንቅናቄ (ኢትዮጵያችን) ልሳን*

ኢትዮጵያችን ቅጽ 3 ቁጥር 3 ታህሳስ ፲፪ ቀን ፪ ሺህ ፲፩ ዓ.ም.

## አቋማችን

(ድምጽ ቅጂውን ለማድመጥ እዚህ ይጫኑ)

"***አንድ ሀገር! አንድ ሕዝብ! ኢትዮጵያችን ሕዝባዊ ንቅናቄ***" በሀገራችን እየተካሄደ ያለውን ለውጥና ወቅታዊ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ሂደቶችን አስመልክቶ ያለንን ዕይታ ለለውጥ ናፋቂው ሕዝባችን እናቀርባለን።

ሥልጣን ከተረከቡ አንድ ዓመት ሊሞላቸው ሁለት ወር የሚጠብቁት የተከበሩ ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድና አጋር አፍቃሪ ኢትዮጵያውያን ወገኖቻቸው የኢሕአዴግን አገዛዝና ሕገ መንግሥት መሠረት አድርገው እየተጓዙና እየነገሩን ያለውን አዎንታዊ ክንዋኔ እያመሰገንን እንደ ፖለቲካ ድርጅት መስተካከል ይገባዋል ብቻ ሳይሆን "አይሆንም፣ ለሀገርና ሕዝብ አይበጅም" የምንለውንም ለማስነበብ ፈለግን።

"***ኢትዮጵያችን ሕዝባዊ ንቅናቄ***" ለአለፉት ሁለት ዓመት ተኩል በየወሩ ባወጣናቸው "***ኢትዮጵያችን***" ልሳን የኢሕአዴግ/ህወሓት አገዛዝን ማንነትና በሀገራችን ኢትዮጵያና ሕዝባችን ላይ ለአለፉት 27 ዓመታት ያደረሰውን ውስብስብ ችግር በመቃኘት መፍትሄውን ጠቁመናል። "የእኛ ጥቆማ ብቻ ነው ትክክለኛና አዋጪ" የሚል ትዕቢት ውስጥ ሳንገባ ሀሳባችንና ጠቋሚ ብዕራችን አልነጠፈም። ጠ/ሚር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ ከሀገር ውጭ ሆነው ለሚንቀሳቀሱ የፖለቲካ ድርጅቶች ወደ ሀገር ገብተው ይንቀሳቀሱ ዘንድ ጥሪ ሲያደርጉ ያስቀመጡት ቅድመ ሁኔታ ቢኖር "ትግሉ ከጦር መሣሪያ ውጭ" መሆኑን ነው። እሰየው ያሰኛል። መቼም ህወሓት ስለ ጦርነት ለመስበክ የሞራል ብቃት ባይኖረውም፤ መሣሪያ አንግበው ትግሉን የገፉ የፖለቲካ ኃይሎችም የየራሳቸውን ዓላማና ፍላጎት ባናነሳም የሰላም በሩ ሲዘጋባቸው፣ በሰላም የታገሉ በመሣሪያ ወደ እስር ሲወረወሩ አማራጭ ከማጣት እንጂ አብዛኛው የፖለቲካ ድርጅት ጦር ናፋቂ ሆኖ አይደለም።

በተደረገውም ጥሪ መሠረት "***ኢትዮጵያችን ሕዝባዊ ንቅናቄ***"ን ጨምሮ በርካታ የፖለቲካ ድርጅቶች ወደ ሀገር ቤት ገብተዋል። "***አንድ ሀገር! አንድ ሕዝብ! ኢትዮጵያችን ሕዝባዊ ንቅናቄ***" ስንመሠረት ይዘን የተነሳነው ለሀገራችን ኢትዮጵያ ያቀረብነው የፖለቲካ ፕሮግራምም ሆነ ማኒፌስቷችን ዛሬም አታጋያችን ነው። ወደ ሀገር ቤትም ስንገባ እራሳችንን ሙሉ በሙሉ ይፋ አድርገንና ከሕዝባችን ጋር ሁነን 27 ዓመት ሙሉ የተሰቃየውን የኢትዮጵያ ሕዝብ መሠረታዊ ጥያቄዎችንና ፍላጎቶች ከግብ ለማድረስ ነው። እኛም ሆንን ሌሎች የፖለቲካ ድርጅቶች ወደ ሀገር መግባት ብቻ የሀገሪቷንና የሕዝቧን ችግር ይፈታል ማለት አይደለም። ገብተን በሀገራችን ምድር ከሕዝባችን ጋር ስንመሠረትም በጨበጥነው ዛሬም ባለቀቅነው የብዕር ጦራችን ለሀገርና ሕዝብ ይበጃል ያልነውን እናሰማለን፣ እናሰነብባለን፤ በሂደትም ወጣቱንና አዲሱን ትውልድ ማዕከል ያደረገ የማደራጀት ሥራችንን

እንቀጥላለን። በማንኛውም መስክ የነገው ሀገር ተረካቢዎች እነሱ ናቸውና። ለ27 ዓመት በኢሕአዴግ/ህወሓት የተጣመመ ታሪክ ፈጠራና ሰበካ የተኮላሸው ኢትዮጵያዊ ብሔራዊ ስሜት ያብብ ዘንድ ይህ አጋጣሚ በቅርብ ሆነን እንድንሠራ በሩን ከፍቶልናልና እንጠቀምበታለን። ኢትዮጵያ ሀገራችን ጠንካራ ተተኪ ትውልድ እንዳይኖራት በተለያየ መጤ ባህሎች የተበረዙትን፣ ተምረው ሥራ አጥ የሆኑትን፣ በኢሕአዴግ የትምህርት ፖሊሲ እንዳይማሩ በአጭሩ የተቀጩትን፣ ከምግብ እጦትና ከቤተሰቦቻቸው አስከፊ ችግር የተነሳ ትምህርታቸው ልመና የሆነውን አሳዛኝ ታዳጊ ወጣቶችን፣ ገላቸውን ሸጠው ቤተሰብ የሚደጉሙትን ሴትኛ አዳሪዎችን፣ በልማት ስም እየተፈናቀሉ በየአስፋልቱ ዳርና ዳር የተከማቹትን በርካታ የህብረተሰብ ክፍሎች፣ ወር ከወር በሰቀቀን የሚኖሩትን የመንግሥት ሠራተኞች ወዘተ አለንላችሁ ከማለት አልፈን ችግራቸውን ተቸግረን ለመታገል ወስነናል። አገዛዙ በረቀቀ መልኩ እናንት የነገ ሀገር ገንቢዎችን በዚህ መልክ ማኮላሸቱ ለነገዋ ኢትዮጵያ መሽመድመድ አቅዱ ነበርና ይህ ያበቃ ዘንድ ወደ ሀገር መግባታችን ጠቅሞናልና በቅርብ፣ ከጎናቸው ሁነን እንታገላለን፣ እናታግላቸዋለን።

በመሆኑም ከብዙው በጥቂቱ የሀገራችንን ወቅታዊ ሁኔታ ስንቃኝ በዚህ መልኩ እናስቀምጠዋለን።

## ታዳጊ ሕፃናት

በየዓመቱ የሚከበረውን የብሔር ብሔረሰቦች ቀን አስመልክቶ ጠ/ሚር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ ከሁሉም አካባቢ በትምህርታቸው ጥሩ ውጤት ካስመዘገቡ ታዳጊ ሕፃናት ጋር ያደረጉት ቆይታና ያሰሙት መልዕክት እሰየው የሚያሰኝ ነው። እነኚህ ከተለያዩ ብሔር/ብሔረሰቦች የተወከሉ የስድስተኛ ክፍል ተማሪ ታዳጊ ሕፃናት በራሳቸው አንደበት እደተናገሩት በዚህ ዕድሜያቸው ከሀገሪቷ መሪ ጋር መገናኘታቸው በውስጣቸው ከሚፈጥረው ስሜት ባሻገር ሲሰበኩ የኖሩብትን ኢትዮጵያን ያለማወቅ አዝማሚያ ለመቅረፍ ጥሩ ጅማሮ ነው። ታዳጊ ሕፃናትና ወጣቶች ላይ ትኩረት ያደረገ የዚህ ዓይነት የማያቋርጥ ተግባር ተዘዋዋሪ ሥራዎች በየክፍለ ሀገሩ ቢከናወኑ 27 ዓመት በወጣቶቻችን ላይ የተሰነቀረውን የዘረኝነት መዘዝ ለማስወገድ ጥሩ አማራጭ ነው። ጠ/ሚር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ ይህንን ተግባር ብቻቸውን ሊወጡት ይከብዳቸዋል፣ ጊዜም አይኖራቸው። ሆኖም ግና ከየአካባቢው/ትምህርት ቤቱ የሚወከሉ ወጣቶችንና ታዳጊ ሕፃናትን ቀደም ሲል ባሳዩት ሂደት ሰብስበው ስለ ኢትዮጵያዊነት እንዲሰብኩና ለኢትዮጵያ ሀገራቸው ዘብ እንዲቆሙ "የኢትዮጵያዊነት ሐዋርያት" ቢያሰማሩ ያለብንን በዘርና/ቋንቋ የመሳሳብ ወያኔ አመጣሽ አገዛዝ ለመቅረፍ ያለው ዕድል ሰፊ ነው። ዛሬ በተለይ አንዳንድ የዘር ድርጅቶች አሁንም ከጠባብ አጀንዳቸው ያልተላቀቁ እንዳሉ እንገነዘባለን። ይህንን አጀንዳቸውን እንዲጥሉ በተማሪዎች፣ በወጣቶችና በታዳጊ ሕፃናት ዘንድ በጠ/ሚሩ የሚመራ ኢትዮጵያዊነት ብሄራዊ ስሜትን የሚያጎለብት ዘመቻ ቢካሄድ - ወጣቶቹ፣ ተማሪዎቹ፣ ታዳጊ ሕፃናቱ የህብረተሰቡ አካል ናቸውና በመጡበትና በተወከሉበት አካባቢ ሊያሳድሩ የሚችሉት ተጽዕኖ ቀላል አይደለም - ይህ ሲሆን በዘር የተደራጁ ድርጅቶች በሀሰት ሰበካ የከበቧቸውን አካላት ያጣሉና - የዚህ ጊዜ ትግላቸው ስለ ኢትዮጵያ በኢትዮጵያ ይሆናል - የሂደቱ መጨረሻም የሁሉም ፍላጎት የሆነው ኢትዮጵያዊነት ያሸንፋል።

## ሙሰኞችና ሌሎች ወንጀለኞች

ሀገራችን ኢትዮጵያ በአለፉት 27 ዓመታት በኢሕአዴግ/ህወሓት አገዛዝ አንጡራ ሀብቷ ተዘርፏል። የሀገሪቷ የኑሮ ውድነት ሊታመን ከሚቻለው በላይ ማሻቀብ የዚህ የዘረፋ ውጤት ነው። ለህሊና በሚሰቀጥጥ መልኩ ከቆሻሻ ማጠራቀሚያ ገንዳ የሚበላ ፍለጋ የሚታየው ሽሚያ ለልማትና ለዕድገት መዋል የሚገባው የሀገሪቷ ገንዘብ ቀን ተሌት በመዘረፉ ነው። የሥራ አጡ ቁጥር መበራከቱ የሥራ

መስክ ሊከፈትበት የሚያስችለው ጥሬ ገንዘብ ወደ ዘራፊዎች ካዝና በመጓዙ ነው። በከተሞችና በየትኛውም ክልል ያለው የውኃ እጥረትና ያላቋረጠ የኤሌትሪክ ኃይል መቋረጥ ለልማት ብድር የሚሰጡ እርዳታዎችና ዶላሮች ወደ አገዛዙ ዘራፊዎች ሆን ተብሎ በመላካቸው ነው። የጎዳና አዳሪዎችና የላስቲክ ቤት ተጋሪዎች መበራከት ቤታቸውና ንብረታቸው በ "ቀን ጅቦች" በመወሰዳቸው ነው። ልቅሶና እግዚኦ ባይ በሀገራችን የየዕለት ተግባር መሆኑ የዘራፊ መንግሥት ሀገሪቷን በመቆጣጠሩ ነው። ከሀገሪቷ በጀትና፣ ከውጭ በእርዳታ መልክና በሌላም ለሀገሪቷ የሚገባውን ነዋይ መዝረፍ አልበቃ ብሏቸው ነጋዴውን በቤት ኪራይና ባልተመጣጠነ ቀረጥ ይዘርፉታል። ጠ/ሚር ዶር ዐቢይ አሕመድን ጣለባቸው እንጂ ከኔ ብጤዎች ላይም ቀረጥ መሰብሰባቸው አይቀሬ ነበር። ይህ ሁሉ አልበቃ ብሏቸው ሕዝብን እያራቆቱ "ሕዝባችን ልመና ይወዳል፣ ቦዘኔነት ጥሞታል፣ መማር አይፈልጉም፣ ሠራተኛውንም መሥራት አይወድም፣ አደገኛ ቦዘኔ፣ ወያላ፣ ፍንዳታ . . ." እያሉ በወጣቶችና በሕዝባችን ስነ ልቦና/ሞራል መጫወትና መሳለቅ የአምባገነኖቹ ተግባርና ባህሪ ነው። "ሕዝብን በረሃብ አድቅቆ መግዛት፣ ከሆዱ ሌላ እንዳያስብ የማስራብ" ፖሊሲ የዘረጋው የኢሕአዴግ/ህወሓት አገዛዝ ዘርፎና ዘራፊዎችን አበራክቶ የሕዝብን እየዬና ዕምባ ያበራከተበት ወቅት ላይ ደርሰናል።

በፖለቲካው ስንኂድ አገዛዙን በመቃወማቸው የታሠሩ፣ የተገረፉ፣ የተንገላቱ፣ አካለ ስንኩል የሆኑ፣ የተገደሉ መበራከታቸው ሀገርና ሕዝብ አውዳሚ አገዛዝ የሥልጣን ባለቤት በመሆኑ ነው። ያሰጉኛል ያላቸውን እያፈነ አጥፍቷል፣ በ"ዱርዬ" የተገደሉ በማስመሰል በአደባባይ ተቀጥቅጠው ተጥለዋል፣ በመኪና አደጋ የሞቱ በማስመሰል የተገደሉም ቁጥራቸው ቀላል አይደሉም። የገዳዮቹ ጉድ ገና መቼ ወጣና። ለምን ፃፋችሁ ተብለው ቤታቸው እስር ቤት፣ እጃቸው ለካቴና የሆኑ ወገኖቻችን ስቃይ አይረሳንም። በአርባ ጉጉና በደኖ የፈሰሰው የንፁሃን ደም ፍትህ ይጠይቃል። የ1997 ዓ.ም. ምርጫ አስታኮ በአደባባይ የተገደሉ ወገኖች፣ ሕፃናትና ወጣቶች ደም ለቤተሰቦቻቸው ብቻ የሚተው ጉዳይ አይደለም። ዘር በማጥፋት መሠሪ ተልዕኮ ደብዛቸው የጠፉ በሚሊዮን የሚቆጠሩ አማራዎች ጉዳይ እንዳይወልዱ መካን የተደረጉትን ጨምሮ ገና ፋይል አልተከፈተለትም። በ27 ዓመት አገዛዙ "እሥር ቤቶች ኦሮምኛ ይናገራሉ" የተባለላቸው የኦሮሞ ወገኖቻችን ስቃይና መከራ በየቦታው እየተገደሉ ለጅብ የተጣሉት ቤቱ ይቁጠራቸው ተብሎ ሚታለፍ አይደለም። በአሸባሪነት ስም በጅምላ ከአየር በቦንብ፣ ከምድር በታንክ የተጨፈጨፉት የምሥራቅ ኢትዮጵያ ኦጋዴንና የኢትዮጵያ ሶማሌ ወገኖች ፍጅት ጊዜው አልፏል፣ ተረስቷል የሚባልለት ጉዳይ አይደለም። ተዘርዝሮ የማያልቅ ገና ብዙ ጉድ ለሕዝባችን ይፋ እንደሚሆን እንጠብቃለን። ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ በቅርቡ እንዳሉት "ዘርፎና ገድሎ መሸሸግ አይቻልም" እኛም እንደግመዋለን።

በጠ/ሚር ዶክተር ዐቢይ አመራር በቅርቡ እየተወሰደ ያለው ዘራፊዎች ላይ ያነጣጠረ የእሥር እርምጃ እሰየው የሚያሰኝ ነው። ያለ አግባብ የሀገርና ሕዝብ ንብረት የዘረፉ፣ ሕዝብንና ልጆቹን ያሰቃዩ፣ ያሠሩ፣ የገረፉ፣ አካለ ስንኩል ያደረጉ፣ ለመካንነት የዳረጉ፣ የስነ ልቦና ጥቃት ሰለባ ያደረጉ፣ ከዚህ ሽሽት ባልፈለጉት አቅጣጫ ተሰደው ሕይወታቸው ላለፈው፣ ሌላም ሌላም አስከፊ ወንጀል ድምጿን ማሰማት የጀመረችው ፍትህ አድማሷን ማስፋት ይኖርባታል። እነሱ ያለፍርድና በግፍ አሰቃይተዋል፣ ገርፈዋል፣ ገድለዋል። ዴሞክራሲያዊ ሂደት ግና በፍትህ ስለፍትህ በሕግ ሊዳኛቸው ይገባል። ሕግና ፍትህ ምን ማለት እንደሆነ ለነበሩትም፣ በቀጣይነት ያሰፈሰፉ ካሉም ሊያውቁት ይገባል። የትላንት ገዳይ በአግባቡ ፍርዱን አግኝቶ ቢሆን የዛሬው ባልተደገመ። "ግደል፣ ዝረፍ ነገ ይቅር እንባባላለን" አባባል እውነት ሁኖ ገዳይና ዘራፊ ሲበራከት እንዳናይ በንፁሃን ዜጎች ላይ ሥልጣናቸውን ተገን አድርገው ለፈረዱ ፍርድ ሊሰጣቸው ይገባል። ይህ ሲሆን ዳግም እንዳይደገም ትምህርት ይሆናል።

## አካባቢያዊ ግጭቶች

*በኢትዮጵያ ሀገራችን እጅግ በአስከፊ መልኩ የተሰበከው የዘረኝነት ስሜት በአንድ አዋጅ ወይም ጦርነት የሚቆም አይደለም። ዘርንና/ቋንቋን መሠረት ያደረገው ህወሓት ጠንሳሹ የኢሕአዴግ ሕገ መንግሥት ለዚህ አስተዋጽዖ አድርጓል። ኢትዮጵያን በዘርና በቋንቋ ከፋፍሎ ለማዳከምና ለመግዛት ካልተቻለ ለመበታተን ተልዕኮው አድርጎ ከጥንስሱ የተዘጋጀው ኢሕአዴግ ዛሬ አመራሩን ኢትዮጵያን ወዳድ ኃይሎች ቢረከቡትም ጠባሳው አልሻረም።* 27 *ዓመት የተተከለው ኢትዮጵያዊነትን ብሔራዊ ስሜት የሸረሸረው የዘርና የቋንቋ ክልልን መሠረት በማድረግ እየተከሰቱ ያሉ አካባቢያዊ ችግሮች ሀገራችንን ወደ አላስፈላጊ የእርስ በርስ ግጭት እንዳይወስዱት የፖለቲካ ድርጅቶች የአቅማቸውን ጥረት ማድረግ ይገባቸዋል።*

*ኢትዮጵያዊነት ተረስቶ ዛሬ ማንነቴ አማራ ነው፣ ኦሮሞ ክልል ማንም ሌላ ድርጅት ሊንቀሳቀስ አይገባውም፣ ትግራይ የዘራፊዎችና የአጥፊዎች ምሽግ ሁና፣ ትላንት በሱማሌ ኦሮሞዎች የደረሰው እልቂት ዛሬ በቤኒሻንጉል እና በሞያሌ እየተደገመ፣ ደቡብ ክልል ግጭቶች እየተበራከቱ፣ ትምህርት ቤቶች በዘር እየተፋጩ፣ የአዲስ አበባ ሕዝብ በፍርሃት ተውጦ ያለውን ሁኔታ እየተገነዘብን የጠ/ሚር ዶክተር ዐቢይ አገዛዝ መደረግ ያለበትን አቅጣጫ መቀየስ ከተሳነው አካሄዱ የከፋ እንዳይሆን ያሰጋናል። ሁሉም በሀገሪቷ ጉዳይ የተሰለፉ ጨምሮ የጠ/ሚሩ አመራር አካላት ለሕዝብ ግልጽ በሆነ መንገድ በሀገሪቷ ያሉ ግጭቶች ላይ ትኩረት በመስጠት ሊመክሩበት ይገባል። የተጀመረው የለውጥ ሂደት ሀገርና ሕዝብ አድን ይሆን ዘንድ በየቀኑ በመንግሥት መገናኛ አውታሮች ሳይቀር እየተዘገቡ ያሉት ግጭቶች ወደ ሌላ አካባቢ ሳይዛመቱና መስመር ሳይስቱ መፍትሄ ሊያገኙ ይገባል።*

*ከጥንስሱ "እኛ ካልገዛናት ኢትዮጵያ ትበታተናለች" ያሉን የቀን አጥፊዎች ሊጫወቱ የሚችሉትን ድብቅ ሚና መናቅ አይገባም። አንዳንድ በዘር የተደራጁ "ነፃነታችንን ማግኛው ወቅቱ አሁን ነው" ደፈጣ በግርግር ያመቻቸው ዘንድ ሊተገብሩ የሚችሉትን ማስተዋል አግባብነት ይኖረዋል። ከጀርባ ታሪካቸው ኢትዮጵያን ለመበታተን በአጋጣሚው ሁሉ የሚጥሩ ወዳጅ መሳይ ባዕዳን እጃቸው ለማን እንደሚዘረጋ መገምገም ያስፈልጋል። በጠ/ሚር ዶክተር ዐቢይ አሕመድና በአቶ ለማ መገርሳ ቡድን ከፍ የተደረገው ኢትዮጵያዊነት አሸናፊ ይሆን ዘንድ መሰናክል ሕጎችና፣ አስተዳደራዊ መዋቅሮች መፈተሽ ይገባቸዋል። አሁን ያለው አመራር ከሥልጣን ርክክቡ ጀምሮ ያገኘውን ሕዝባዊ ድጋፍ ሊጠቀምበት ይገባል። ከሕዝባዊ ድጋፉ ይልቅ ሀገሪቷን ቀፍድዶ የያዘው አሠራርና አወቃቀር ጠቅለል ባለ መልኩ* 27 *ዓመት የነበረው ሥርዓት ካደላበት ጉዞው ሁሉ የዕምቧይ ካብ እንዳይሆን እንሰጋለን።*

## ምርጫና የፖለቲካ ድርጅቶች ውህደት

*"**አንድ ሀገር! አንድ ሕዝብ! ኢትዮጵያችን ሕዝባዊ ንቅናቄ**" የኢትዮጵያንና የሕዝባችንን መሠረታዊ ችግሮች የሚቀርፍ አቅጣጫ ሰጪ ሠነድ ለመንደፍ የሁሉን የፖለቲካ ድርጅቶች የጋራ መግባቢያ የውይይት መድረክ አስፈላጊ መሆኑን እናምንበታለን። እውነት ለመናገር ዛሬ ስለ ምርጫ ሳይሆን የሀገር ሉዓላዊነቷና የሕዝባችን አንድነት እንዳይናጋ ተግተን የምንሠራበት፣ የምንመክርበት ካስፈለገም ለመስዋዕትነት ዝግጁ የምንሆንበት ወቅት ላይ ለመሆናችን "መረጋጋት ያለው የት ነው?" ብሎ መጠየቁ በቂ ነው። የዜና አውታሮች ተባረሩ፣ ተፈናቀሉ፣ ተሰደዱ፣ ተገደሉ የሚል ዜና እየዘገቡ፣ ጆሮዎች ይህን እየሰሙ፣ በሶሻል ሚድያዎች የዘር ፉክቻዎች እየጦዙ "አኩሪ ሰላም" ያለ ይመስል ስለ ምርጫ ጊዜ የሚጠፋበት ወቅት አይደለም። ምርጫን ታዛቢ፣ አስከባሪ፣ አስፈጻሚ፣ ተመራጩን ተቀባይ፣ መራጩን አስተናጋጅ ሀገር ናትና። መቅደም ያለበት ባልተሸፋፈነ መልኩ ያለውን ችግር ሀገሩ ናትና ሕዝብ አውቆት በመላ ሀገራችን አስተማማኝ ሰላም እሚገኝበት ላይ ማተኮሩ ይገባል።*

በሌላ በኩል የፖለቲካ ድርጅቶች ውህደት በትዕዛዝ የሚተገበር አይደለም። በ27 ዓመት የፖለቲካ ድርጅቶች ታሪክ እንኳንስ አንዱ ድርጅት ከሌላው ተባብረው መሥራት ይቅርና በአንድ ድርጅት ደረጃ ያለውን አለመግባባት፣ ሽኩቻ ብሎም መከፋፈል ተገንዝበናል። አሁንም ቢሆን እውን ጉዟችን ለግል ሥልጣንና ዝና ካልሆነ ለሀገርና ሕዝብ ሲባል በተለይ በኢትዮጵያ ሀገራዊ አንድነት ላይ የማያወላዳ አቋም ያላቸው ኅብረ ብሔርም ሆኑ የዘር ድርጅቶች በጋራ ሊመክሩና በጋራ አግባቢ ሠነድ ላይ አብረው ሊሠሩ ይገባል። በተለይ ዛሬ በተፈጠረው የሀገራችን የለውጥ ጭላንጭል በአካል ለመሰብሰብ፣ ለመነጋገር፣ ለመወያየት ያለውን ዕድል ተጠቅሞ በጋራ መምከር መጀመሩ በቀጣይነት ለሚደረግ ህብረትም ሆነ ውህደት በር ከፋች ነውና ሊታሰብበት ይገባል። "ዕድሉ የእኛ ነው" ብሎ ለሥልጣን ኮርቻ መሽቀዳደም ነፍሱን ይማረውና ገጣሚ ገመራው እንዳለው "ዜሮ አያ ድቡልቡል" እንዳይኮን። ከዚህ በፊት የተመሠረቱ ኢድኃቅ፣ አማራጭ ኃይሎች፣ ቅንጅት፣ ህብረት፣ . . . መክሰም በጠንካራ መሠረት ላይ አለመገንባታቸው፣ አለመዋቀራቸው ውጤት ነው። የፖለቲካ ድርጅቶች ጠ/ሚር ዐቢይ አሕመድ ጥሪ አድርገውላቸው ኢትዮጵያ ከመግባታቸው በፊት የነበሩት ሸንጎ፣ የኢትዮጵያ ሀገራዊ ንቅናቄ፣ የሲያትሉ 26 ድርጅቶች ትብብር፣ የት ደረሱ? ዛሬ ደግሞ እኛም "***ኢትዮጵያችን ሕዝባዊ ንቅናቄ***" አባል የሆንበት የ 7 ፖለቲካ ድርጅቶች የውህደት ሂደት ለዜና በቅቷል። ይህ ብሥራተ ዜና ቀደም ሲል የጠቀስናቸውን ስብስቦች (ሸንጎ፣ የሲያትሉ ጉባኤ ተሳታፊዎች፣ ኢትዮጵያ ሀገራዊ ንቅናቄ) እና ሌሎችን አካቶ ቢጠናከር ፍላጎታችን ሀገርን ማዳን፣ ለሕዝባዊ ጥያቄ ምላሽ ማስገኘት ከሆነ አስፈላጊ ነው። ይህ ሲሆን የኢሕአዴግ አገዛዝ ጠንካራ ተፎካካሪ ማጋጠም ብቻ ሳይሆን ሀገሪቷን ቆላልፎ የያዘበት አፋኝ ሕግና ሥርዓት ይሻሻላል አለያም ያከትምለታል።

## ኢትዮጵያዊ ዜግነት

በዓፄ ኃይለ ሥላሴ ዘመን ወደ ውጭ ሀገር ለትምህርት የተላኩ ኢትዮጵያውያን ትምህርታቸውን ጨርሰው አንድ ቀን መቀመጥ እየተሳናቸው ወደ ሀገራቸው እንደሚመጡ ይነገር ነበር። የትምህርት መረጃቸውን (ሰርተፊኬት፣ ዲፕሎማ፣ ድግሪ ሌላም) እንኳ ላኩልን እያሉ እስኪዘጋጅላቸው ትዕግስት የላቸውም ይባላል። በ1966 ዓ.ም. የለውጥ ማዕበል ትምህርትና ሥራቸውን እያቋረጡ ወደ ሀገር የገቡ እጅግ በርካታ እንደነበሩ አይዘነጋም። የዚህ ነፀብራቅ ታዲያ የትም ቢሆን ኢትዮጵያዊ ሀገሩን ወዳድ ሕዝቡን አፍቃሪ መሆኑን ነው።

ጊዜና ፖለቲካ ለአምባገነኖች አደላና በትንሹ ለአለፉት 44 ዓመታት ኢትዮጵያና ልጆቿ የሁለት አገዛዞች መከራ ተቀባይ ሆነች። ስደት የኢትዮጵያውያን ዕጣ ፈንታ ብቻ ሳይሆን ባዕድ አፍቃሪ ትውልድ እንዲበራከት አስተዋጽዖ አደረገ። ሀገራቸውን ጥለው የተሰደዱ ለኑሮ፣ ለትዳር፣ ለሌላም ሲባል ዜግነት መቀየር ግድ ሆነባቸው። ሀገራቸው የምትናፍቃቸው ወደ ሀገር ሹልክ ብለው ለመመለስም አማራጩ ዜግነት መቀየር በመሆኑ የግድ ተቀበሉት። ያም ሆኖ በዚህ 27 ዓመት የኢሕአዴግ ብልሹ አገዛዝ በውጭው ዓለም ያሉት ኢትዮጵያውያን ሳያሰልሱ ለሚደረገው ሕዝባዊ ትግል ድምጻቸውን አሰምተዋል ዋና የድጋፍ ምንጭ ሆነዋል። በየኤምባሲው፣ በየኮንግረስ ጽሕፈት ቤት፣ በአገኙት አጋጣሚ ሁሉ ስለ ኢትዮጵያ የጮኹት በውጭ ያሉት ኢትዮጵያውያን ናቸው። እንኳን የተሰደዱት በውጭ ሀገር የተወለዱ ሕፃናት ሀገራቸው ኢትዮጵያ ትናፍቃቸዋለች፣ ታሳስባቸዋለች። ሀገራቸውን ጠልተው ሳይሆን ሁኔታዎች አስገድዷቸው ዜግነታቸውን የቀየሩ በርካታ ናቸው።

የህወሓት/ኢሕአዴግ ሕገ መንግሥት መቀየር ያለበት ከፋፋይ ሕገ መንግሥት ነው ብለን የምንቃወመው ሀገርን በዘርና በቋንቋ መሸንሸኑ ብቻ ሳይሆን ስለ ኢትዮጵያ ዜግነትም የሁለት ዜግነትን (Dual citizenship) አለመፍቀዱ ነው። ይህ ደግሞ የመለስ ዜናዊ አገዛዝ ሲፈጠርም በውጭ ያለው ዲያስፖራና ፖለቲከኛ በሀገር ቤት ምንም እንቅስቃሴ እንዳይኖረው ፈላጊ ነበርና ይህንን በሕገ መንግሥቱ አሠፈረው። ዛሬም "ሥጋ ሰጥቶ ቢለዋ መንሳት" እንዲሉ ጠ/ሚር ዶክተር ዐቢይ "ፓስፖርታችሁን ቀዳችሁ ግቡ፣ የሕገ መንግሥት ጉዳይ ነው" በሚል ማንም ኢትዮጵያ ፓስፖርት የሌለውን ፖለቲከኛ በሀገሩ ጉዳይ ገደብ እንዲጣልበት ሲፈርጁ አስገርሞናል። ዛሬ ከውጭ ፖለቲካ ድርጅቱን ይዞ የገባው ተፎካካሪ ፖለቲከኛ ከረዥም ዓመታት የውጭ ኑሮ የተነሳ በአብዛኛው የውጭ ሀገር ዜግነትን ተላብሷል። ይህ እየታወቀ የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል ይመስል ሕገ መንግሥት፣ ሕገ መንግሥት ሲባል ትግሉ ገና ብዙ እንደሚቀረው መገንዘብ ይቻላል። ይህ ተደራቢ ዜግነት (Dual citizenship) ጉዳይ በአፍሪካ እንኳ ከ10 በላይ ሀገራት ተግባራዊ ያደረጉት አዲስ ነገር አይደለም።

ለሀገራችን ልማትና ዕድገት ሲባል አግባብነት ባለው መልኩ ከውጭ ባለ ሀብቶችና ኩባንያዎች ጋር የሚደረጉ የተለያዩ ኢኮኖሚያዊ ትስስር የሚደገፍ ቢሆንም ትልልቅ ተቋማትን (የኤሌክትሪክ ሃይል፣ የቴሌኮሚኒኬሽን፣ የአየር መንገድ ተቋማትን)፣ መንግሥታዊ ፕሮጀክቶችን፣ ግንባታዎችን፣ የተፈጥሮ ሀብትና የማዕድን ክምችቶችን፣ ወዘተ በውጭ ኩባንያዎችና ዜጎች እያስወረሩ ለእኛ የኢትዮጵያ ልጆች "ፓስፖርታችሁን ቅደዱ" ማለት አሁንም የውጭውን ፖለቲከኛ ሞራል ለመንካት ካልሆነ በቀር አግባብ አይደለምና ሊታሰብበት እንደሚገባ እንጠቁማለን።

## <u>ውድ የኢትዮጵያ ሕዝብና ታዳጊና ወጣት ልጆቿ</u>

እጅግ ለበርካታ ዓመታት ኑሯችሁ ረሃብ፣ ጓደኛችሁ መከራ፣ ቤታችሁ እሥር ቤት፣ ሕይወታችሁ ሞት ሁኗል። እምነት ያላችሁ በፀሎቱ አምላኬ ሆይ! የአላህ! ብላችሁ ስለ ሀገራችሁና እምነታችሁ ተማጽናችኋል። ቀደም ሲል በልጆቻችሁ ቀጥሎም በልጅ ልጆቻችሁ ተመሳሳይ ስቃይ የተቀበላችሁ የትላንት እናቶች/አባቶች የዛሬ አያቶች እውን ምን ይሰማችሁ? ትላንት ወንድማችሁን/እህታችሁን ዛሬ ባለትዳር ሁናችሁ ልጆቻችሁን ለመከራ፣ ለስደት፣ ለግርፋት፣ ለሞት ያስረከባችሁ የትላንት ወጣቶች የዛሬ እናቶች/አባወራዎች ምሬታችሁ በምን ይገለጻል? በሁለት አገዛዝ አምባገነናዊ ጥይት ልጆቿን ያጣች ሀገር ምነዋ ወደ አምላኳ የዘረጋችው እጆቿን የሚጨብጣት አጣች? ምነዋ የነብዩ መሐመድ "ኢትዮጵያን አትንኳት" ቃል ኪዳን ሰሚ አጣ?

ዛሬ የሕዝብ ትግል ውጤት የሆኑት ጠ/ሚር ዶክተር ዐቢይ አሕመድና የአቶ ለማ መገርሳ ቡድንና አፍቃሪ ኢትዮጵያውያን ድምጽ "ተመስገን! አሁን ፀሎታችንን ሰማን" ያላችሁት አምላክ አሁንም መጨረሻውን ያሳምርልን እንላለን። አምላካችንን ዘንግተን የመጣብን ቅጣት ከሆነም የታቦቶቹን ቁጥር ያህል 17 ዓመት በደርግ 27 ዓመት በኢሕአዴግ በጥቅሉ 44 ዓመት የተቀጣነው ይበቃን ዘንድ ምሕረቱን ይላክልን። ሰውማ ምን ያህል ግፍ ፈጻሚ እንደሆነ ሰሞኑን ለአየር የበቃው የእሥረኞች ልቅሶ መስካሪ ነው።

ይህ ሁሉ መከራና ግፍ ያበቃ ዘንድ በተለይ የሀገራችን ወጣቶች ከፍተኛው ኃላፊነት ይጠበቅባችኋል። ግድያንና ዝርፊያን እንዳትወርሱ። ስለ ሀገር መጮህ፣ ለሰንደቅ ዓላማ ክብር መስጠት፣ ለሕዝባችሁ የገደል ማሚቶ መሆን ይጠበቅባችኋል። በአምባገነን ገዥዎች የተጣለባችሁን መከራ ለማራገፍ ችግርን አትፍሩት፣ ግድያን ለማቆም መግደልን ሳይሆን መስዋዕትነትን ተማሩ። የዚህ ጊዜ አሸናፊው እናንተና ሀገራችሁ ናትና ለኢትዮጵያ ስለ ኢትዮጵያ ስትሉ በርቱ። የኢትዮጵያ ሕዝብ ለበርካታ ዓመታት እየደረሰበት ያለው ግፍና መከራ ለነገው ትውልድ እንዳይሻገር በእኛ ይብቃ እንላልን።

**ኢትዮጵያ ለዘለዓለም ትኑር!**
**እግዚሐብሔር ኢትዮጵያን ይባርክ!**
**አንድ ሀገር! አንድ ሕዝብ! ኢትዮጵያችን ሕዝባዊ ንቅናቄ**
**ታህሳስ 12 ቀን 2011 ዓ.ም. December 21, 2018**

**ማሳሰቢያ ፡**

- ውድ ወገኖቻችን ይህንን "አንድ ሀገር! አንድ ሕዝብ! ኢትዮጵያችን ሕዝባዊ ንቅናቄ" «***ኢትዮጵያችን***» ዕትም በተለይ በሀገር ቤት ኮምፒዩተር የማግኘት ዕድል ለሌላቸው በማባዛት ታሰራጩት ዘንድ ቀና ትብብራችሁን በትህትና እንጠይቃለን።
- "አንድ ሀገር! አንድ ሕዝብ! ኢትዮጵያችን ሕዝባዊ ንቅናቄ" መስከረም 8 ቀን 2009 ዓ.ም. እራሱን ይፋ ያደረገ ሕዝባዊ ድርጅት ሲሆን የንቅናቄውን ማንፌስቶና ፕሮግራም www.ethiopiachen.org ከሚለው ድረ ገጻችን ማግኘት ትችላላችሁ።

ስልክ፡ 703 300 4302

ኢሜል ፡ ethiopiachen2009@gmail.com
info@ethiopiachen.org
ድረ ገጽ ፡ www.ethiopiachen.org
www.ethiopiachen.com
ምሥለ ገጽ ፡ 1H1H Ethiopiachin